በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአውሮፓ አህጉረ ስብከት
THE ETHIOPIAN ORTHODOX TEWAHEDO CHURCH ARCHDIOCESES IN EUROPE

---

**ጸልዩ በእንተ ሰላመ ቤተ ክርስቲያን አሐቲ ቅድስት ጉባኤ እንተ ሐዋርያት ርትዕት. በኃበ እግዚአብሔር።**

- **ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ፓትርያርክ ርዕሰ ቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት**
- **ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት**
- **ለብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት**
- **ለመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት**

**አዲስ አበባ ኢትዮጵያ**

- **ለሁሉም ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት**

**በየአሉበት**

**ጉዳዩ ፤ የ፳፻፲፪ የርክበ ካህናት ቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤና ወቅታዊው የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የገጠማትን ተግዳሮት ይመለከታል።**

በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ ፳ ቁጥር የ፲፳ የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ በዓመት ሁለት ጊዜ እየተሰበሰበ ሃይማኖትን ለማጽናት፣ ምግባርን ለማቅናት ፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለማስፋት፣ ምእመናንን ለማብዛት ፡ ሕግንና ሥርዓትን ለማውጣት ብሎም ለማስፈጸም ፡ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሁለንተናዊ አንድነት ለማጽናትና ሁለንተናዊ ጥቅሟን ለማስጠበቅ መብቷን ለማስከበር አስተምሕሮዋን ለማስፋት እና ለማስቀጥል ፣እንዲሁም ለምእመናን አንድነት፣ ለአገር ሰላምና ደኅንነት የሚጠቅሙ ውሳኔዎችን የሚያስተላልፍበት ምልዓተ ጉባኤ ነው።

እንደሚታወቀው ሀገራችን ኢትዮጵያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ መሆኗ ይታወሳል ፣ ቤተ ክርስቲያናችንም የእዚሁ የመከራ ጽዋዕ ዋና ቀማሽ ከሆነች ውላ አድራለች ፣ ይህ ችግር ተባብሶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የሚመራው የቅዱስ ሲኖዶስ ህልውናው የሆነው አንድነቱን የሚፈታተንና ግልፅ ተግዳሮቶች እንደገጠማትና ብዙዎቻችንን የሕሊና ዕረፍት የነሳን ጉዳይ ነው።

ከአሁን በፊት በየክልሎቹ የጳጳሳት ሢመት ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ውጪ መፈጸሙ ፣የደረሰው ስብራት በውል ሳይታከም ፣ በቅርቡ ደግሞ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ፀሐፊን ጨምሮ ሌሎች ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት ግንቦት ፲፩/፳፻፲፪ በሚደረገው የርክበ ካህናት የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ላይ ምክንያቱ ግልጽ ባልሆነ ሁኔታ መገኘት እንዳይችሉ መደረጉን ለማወቅ ችለናል።
በመሆኑም እኛ በአውሮጳ የምንገኝ በአራቱ አኅጉረ ስብከት የምንገኝ ካህናት ፣ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ፣ ምእመናን እና ምእመናት በሙሉ ፣ቅዱስ ሲኖዶስ በምልዓተ ጉባኤው በጽሞና ይመለከታቸው ዘንድ የሚከተለውን መግለጫ አውጥተናል ።

፩/ እጅግ አሳሳቢ የሚሆነውና ቅድሚያ በዋና አጀንዳነት በመያዝ የሲኖዶሱን አንድነትና ልዕልና ማስጠበቅ ተገቢ በመሆኑ ቅዱስ ሲኖዶሱ ሁሉም የብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በምልዓተ ጉባኤው ላይ የሚገኙበትን ሁኔታ እንዲመቻች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተወይይቶ መፍታት የሚችልበትን መፍትሔ እንዲያዘጋጅ እንጠይቃለን።

፪/ እስካሁን በተገነዘብነውና በተረዳንነው የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊና ሌሎችም ሊቃነ ጳጳሳት ለርክበ ካህናት የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ እንዳይገኙ የተደረገበት ሁኔታ ምክንያቱ ግልጽ ባለመሆኑ፣ ይህ የቅዱስ ሲኖዶሱን አንድነት የሚፈታተን ከባድ ችግር ሊያስከትል ይችላል የሚል ሥጋት ስለአለን፣ ከወዲሁ መፍትሔ ሳያገኝ ስብሰባ ማድረጉ ከጥቅሙ ጉዳቱ ስለሚያመዝን፣ ስብሰባው ለሌላ ጊዜ ተላልፎ እግዚአብሔር አምላክ ይረዳን ዘንድ ቅዱስ ሲኖዶስ የምሕላና የጸሎት ዐዋጅ ቢያደርግ።

፫/በቅዱስ ሲኖዶስ አባላት መካከል ልዩነቶችን የሚፈጥሩ ፣ እንዲሁም አንድነት ከሚከፋፍሉ አጀንዳ አራማጅ አካላት ፣ ከዚሁ ድርጊታቸው እንዲቆጠቡ እያሳሰብን ፣ እኛም እንዲህ ዓይነት እኩይ ተግባራትን የሚያደርጉትን በመከታተልና በማጋለጥ ለሕዝቡ እውነታውን ለማስረዳትና ለማሳዎቅ የቡኩላችንን ድርሻ እንደምንወጣ ለማሳዎቅ እንወዳለን።

፬/በመጨረሻም በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤው የሚወሰኑ ውሳኔዎች ልዩነትን በመተው ቅድሚያ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት አንድነት ላይ ያተኮረ ውይይት በማድረግ በጸሎት ሕዝበ ክርስቲያኑን በማጽናናት እና የተለያዩ የውስጥ ክፍተቶችን በመፍታት ላይ ያተኮረ ውይይት በማድረግ እንዲያሳልፍ እየጠየቅን እኛም በቅዱስ ሲኖዶስ የሚሰጠው ውሳኔ ተግባራዊ ለማድረግ የበኩላችንን ድርሻ ለመወጣት ቃል እየገባን። ፣ አምላካችን ቤተ ክርስቲያናችንንና አባቶቻችንን ይጠብቅልን፤ እኛንም ለአባቶች የሚታዘዝ ልቡና፣ ሓላፊነታችንን የምንወጣበትን ጥበብና ማስተዋሉን ያድለን ዘንድ እግዚአብሔር አምላክ ይርዳን።

በአውሮጳ የዐራቱ አህጉረ ስብከት አንድነት

- ጀርመንና አካባቢው ሀገረ ስብከት
- ጣሊያን እና አካባቢው ሀገረ ስብከት
- ስዊድን ፣ስካንዲናቪያን እና ግሪክ ሀገረ ስብከት
- ዩናይትድ ኪንግደምና አየርላንድ ሀገረ ስብከት
  አውሮጳ